# የአቶ ዘርዑ ክሕሸን አጭ ር የህይወት ታሪክ

አቶ ዘርዑ ክሕሸን እ አ አ መ ጋቢት 23, 1942 ዓ ም በትግራይ ክፍለ ሃገር ሀሌ በሚኮሩባት በዓጋመ አወራጃ በአዲግራት ከተማ ልዩ ስሟ ዓዲ አመቀክርስቶስ በምትባ1 መንደር ወሰጥ ተወለዱ።

የትምሕርት እድሜአቸው እንደደረሰ የአንደኛ ደረጃ ትምሕርታቸውn ዓዲግራት በሚገኘው አግአዚ ትምሕርት ቤት አጠናቀቁ። ከዚያም የሀለተኝ ደረጃ ትምሕርታቸወን በቅድሚ ያ መቀሌ በሚገኘው አፄ ዮሐንስ ሀለተኛ ደረጃ ትምሕርት ቤት ጀምረው አዲስ አበባ ከነበረው ቀ ኃ ሥ ሀለተኛ ደረጃ ትምሕርት ቤት ሰኔ 1961 ዓ/ም በ B A ዲግሪ ተመረቁ,

አቶ ዘርዑ የመጀመሪያ ዲግሪአቸወን ለማገኘት ይህን ያክል ጊዜ ለፈጀባቸው የቻለበት ም ክንያት በዚያን ጊዜ ብቸኛ የኢትዮጵያወያን የብሲት ደምፅ በነበረው የተማሪዎች እንቅስቃሴ ከነበሩት እው ቅ መሪዎች አንዱ ስለነበሩ በየጊዜው ይታሰሩና ከትምህርት ገበታቸው ይባረሩ ስለነበር ነ ው።

ቀጥለው በ 1973 ዓ/ም የ M A ዲግሪአቸው ን በኢኮኖሚ ክስ ከ City University of New York እንዳገኙ እዛው ዩንቨርሲቲ የዶክትሬት ጥናታቸው ን ቀጠሉ።

እዛው ሆነ ው በተለይ የሰሜኑ አሜሪካ ተማሪዎች ማ ህበርን በማ ደራጀት በከል ብዙ ጥረት ከማድረጋቸው ም ሌላ የኢትዮጵያን ጉዳይ በሚ መ ለከት በአዲስ አበባና ሌሎች አካባቢዎች የነበሩትን ኢትዮጵያወያን ትግላቸወን በማ ቀናጀት ይረዱ ነበር። በመ ሃከሉ ግን ኢትዮጵያ ው ስጥ ይካሄዱ የነበረው የለወጥ እንቅስቃሴ ከቀን ወደ ቀን እያየለና እያደገ በመ ም ጣ ቱ ትምሕርታቸወን አቋርጠው ወደአዲስ አበባ ተመለሱ።

ከዚያም የተቀጣጠለው ን የለው ጥ ማ ዕበል መሪ አልባ እንዳይሆንና የሕዝቡ ትግል የተደራጀ መልክ እንዳይዝ ለማ ስቻል ኢሕአፓን በመ መ ስረት፤ በማ ደራጀትና በመምራት በዚሁ ድርጅት አማካኝነ ትም ሜሬት ላራሹ ይሰጥ፥ ሕዝባዊ መንግስት ይቋቋም ፥ ዲሞክራሲያዊና ፍትሃዊ ሥ ርዓት ይመ ስረት ወ ዘተ የሚ ሉ የትግል መ ፈክሮች ና እምነ ቶች በሃገሪቱ ከጫ ፍ እስከ ጫ ፍ እንዲስተጋቡ በማድረግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል።

በሌላ በከል ደግሞ በዚያን ወቅt የሀለት ልጆቻቸው የገብሬይና የሰላም እናት ከሆኑት ከመ ጀ መሪያ ባለቤታቸው ና በትግል ለረጅም ጊዜ አብረዋቸው ከተሰለፉት ከወይዘሮ ታደለች ኪዳነ ማርያም ጋር የጎጋበዙበት ወቅት ነበር።

አቶ ዘርዑ ክህሸን ከትግል ሕይወታቸው ጋር እያጣ መ ሩ በሥ ራ መስክ በአስተማ ሪነ ት፤ በኢትዮጵያ አየር መንገድና በብሔራዊ ሀብት ደግሞ የኢኮኖሚ የጥናት ኢክስፐርት በመሆን እንዲሁም መጀመሪያ ገደማ ደርግ ባቋቋማቸው ኮሚቴዎችና ግብረ ኃይሎች ወስጥ የብ ሔ ራዊ ጊዳይና በብሔራዊ ደረጃ የህብረተሰብ ችግሮችን በሚ መለከት ለመንግስt አጥንቶ የሚ አቀርብ ኮሚ ቴ አባል ነበሩ።

ሆኖም ደርግ ይከተለው የነበረው ሥ ርአት ከእምነ ታቸው ጋር ሊጣጣም ባለመቻሉ ረዘም ላለጊዜ በአዲስ አበባና በሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች ሆነ ው የደርግን መንግስት በመቃወም ሲታገሉ ነበር።

ከዚያ በኋላ ግን አገር ቤት የነበረው የትግል መልክና ሁኔታ በሚያምኑበት መንግድ ሊሄድ ባለመቻሉና የጤ ንነ ታቸው ሁኔታ አስጊ ደረጃ ላይ ደርሶ ስለነበር የሚ ወ ዱ ትንና ዕድሜ ልካቸወን የታገሉለትን አገርን ሕዝብ ትተው ከ 1979 ዓ/ም ጀምሮ በስደት በአምስተርዳም ከተማ ወስጥ መኖር ጀመሩ።

በዚህ የአመስተርዳም የኑሮ ጊዜአቸው በአምስተርዳምዋ ዩንቨርሲቲ በኢኮኖሚክስ የዶክተር አንዱስ ዲግሪ በልዩ ማ ዓረግ ካገኙ በኋላ በፍራይ ዩንቨርሲቲ በኢኮኖሚ ክስ የጥናት ኢክስፐርት ሆነ ው ለብዙ ጊዜ ሰሰሩ ቆይተዋል።

ባለፈው ጥቂት ዓመታት ደግሞ የአሁኗ ባለቤታቸው ወይዘሮ ቲምና ቫንዳምን ከተዋወቁበት ጊዜ ጀምሮ ተጋብተው አንድ ላይ በኖሩበት የጋብቻ ሕይወት እጅግ ደስተኛ እንደነበሩና ለባለቤታቸው የተለየ ፍቅርና አክብሮት እንደነበራቸወም ደጋግመው ይናገሩ ነበር።

አቶ ዘርዑ ባለፉት 30 ዓመታት የተሟ ላ ጤ ንነ ት አልነበራቸወም ። ሃኪሞችም በየጊዜው የቀራቸው ሕይወት በጥቂት ወራት የሚ ቆጠር መሆኑን ደጋግመው ይነ ግሩአቸው ነበር።

አቶ ዘርዑ ግን ይህንን ሁሉ በመቋቋም ከፊታቸው ፈገግታ ቀልደና ጨዋታ ሳይለይ የወገንና የሃገር ጽኑ ፍቅራቸው እንዳለ ሆኖ በዓላማቸው እንደጸኑ ጠንካራወና ቆራጥ የታጋይ መንፈሳቸው ሳይነካ ከትምህርትና ከሥራም ዓለም ሳይለዩ ቆይተዋል።

በትግሉም በኩል ቢሆን የጤንነት አቅማ ቸው በፈቀደላቸው ማጠን እስከ እለተ ሞታቸው ድረስ ስለአገርና ወገን ሲጨነቁና በተለይ የሃገራችንን ሉዓላዊነትና የድንበር ጉዳይን በተመለከተ ደግሞ ሃሳባቸውን በጽሁፍና በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን አማካይነት ይገልጹ ነበር።

የአቶ ዘርዑ ክሕሸን የሕይወት ታሪክ ለወደፊት በሰፊው እንደሚገለጽና በኢትዮጵያ የትግል ታሪክ ወስጥ አንድ ራሱን የቻለ ትልቅW ምዕራፍ እንደሚኖረው ሁሉም የሚ አወቀው ነው ።

ከቤተሰቡ እና ጓደኞቻቸው